# ጀፈርሰን ሂውስተን (Jefferson Houston) - የወላጅ እና ቤተሰብ ተሣትፎ ፖሊሲ
# 2025-2026

የጀፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK8 IB ትምህርት ቤት፤ በተማሪዎች የቀለም-ትምህርት ስኬታማነት ላይ፣ የወላጅ ተሣትፎ - ወሳኝ-ሚና መኖሩን ከፍተኛ-ዋጋ የሚሰጠው ነው። ጀፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) - ከወላጆች ጋር መተባበር በእውነቱ በተቻለ-መጠን በከፍተኛ ደረጃ ስለመሳተፍ-የሚገልጽ መሆኑን፣ እና ወላጆች - የተማሪዎቻቸው ትምህርት-ላይ በመርዳት ላይ ወሳኝ-የሆነ ሚና እንደሚጫወቱ ያምናል።

1. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ ላይ፤ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ ወላጆች ይበረታታሉ
2. በልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ ላይ፤ ወላጆች፣ ሙሉ-አጋሮች በመሆን እና እንደ-ተገቢነታቸው - በውሳኔ አሰጣጥ እና በልጆቻቸው ትምህርት ላይ እገዛ ለማድረግ በአድቫይዘሪ ኮሚቴዎች ውስጥ ይካተታሉ

<u>የዕቅድ አወጣጥ፣ ሂደት</u>

የጀፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK – 8 IB ትምህርት ቤት፣ ይህን የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲን - ከትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ማህበረሰብ አባላቶች፣ እና ወላጆች ጋር በመማከር፣ በጋራ-ሆነው አዘጋጅተዋል። ይህ ፖሊሲ፤ ለወላጆች - በሚመርጡት ቋንቋ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። ይህ ፖሊሲ፤ በትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽ፣ በኢሜል እና በበራሪ-ወረቀት (newsletter) ላይ፣ ለወላጆች እና ለአካባቢው ሁብረተሰብ እንዲዳረስ ይደረጋል። የ‘Title I’ ዕቅድ/plan (application) ለወላጆች አጥጋቢ ካልሆነላቸው፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዕቅዱን ከ‘application’ ጋር ለስቴቱ ሲያስገባ፣ የማንኛውንም ወላጅ አስተያየቶች አብሮ ያስገባል። የወላጆች ተሳትፎ እቅድ፣ የወላጆችን እና የትምህርት ቤትን - ተለዋዋጭ የሆነ ፍላጎቶችን ለማሟላት፣ በየዓመቱ አዲስና ማሻሻያ (updated) ያደርጋል።

<u>ትምህርት ቤት እና ቤተሰብ - ጥምረት **(COMPACT)**</u>

የጀፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK – 8 IB ትምህርት ቤት እና በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚማሩ-ተማሪዎች ወላጆች፤ ይህ የጥምረት ዝርዝር (compact outline)፣ ወላጆች፣ አጠቃላይ ትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ እና ተማሪዎች - የተማሪውን የቀለም ትምህርት ስኬትማነት ለማሻሻል እና፣ ትምህርት ቤት እና ወላጆች - ልጆች የስቴቱን ከፍተኛ ደረጃዎች/high standardsን እንዲያገኙ በሚረዳቸው ነገሮች ላይ ለመገንባት እና አጋርነትን ለማሳደግ፣ ያላቸውን ኃላፊነት እንዴት እንደሚያጋሩ ይዘረዝራል። ይህ የትምህርት ቤት-ወላጅ ጥምረት (compact)፤ ለትምህርት ዓመት 2025-2026 በስራ ላይ ውሎ-የሚያገለግል ነው።

## <u>የትምህርት ቤት ስምምነት</u>

የ‘ጀፈርሰን-ሂውስተን **(Jefferson - Houston)** ከ**PreK – 8**ኛ **IB** ትምህርት ቤት’ - የሚከተሉትን ያደርጋል:

- ከአሌክሳንድርያ ከተማ ስልታዊ ዕቅድ **(Strategic Plan)** ጋር ጎን-ለጎን በመሆን - የጀፈርሰን-ሂውስተን **(Jefferson - Houston)** ከ**PreK-8**፤ ሁሉን-ተቀባይነት፣ ኃይልና-ጉልበት ሰጪ፤ ፍትሃዊነት ላይ-ትኩረት ያደረገ፣ ፈጠራዊ-የሆነ **(Innovative)** እና ውጤቶች-ላይ ተኮር በመሆን፣ ዋናውን ዕሴት **(core values)** በመከተልና ተገዢ-በመሆን ይሰራሉ።
- ከፍተኛ ጥራት ያለው ስርዓተ-ትምህርት እና የትምህርት አሰጣጥን፤ ድጋፍ-ሰጪና ውጤታማ የመማሪያ አካባቢ ውስጥ - ተሳታፊ ተማሪዎች የስቴቱ/**state**ን የትምህርት ብቃት-ደረጃን እንዲያሟሉ ለማስቻል፣ የሚከተሉትን ያከናውናል:
    - በመማሪያ-ክፍል ውስጥ፣ የሚያበረታታ እና ፍላጎትን-የሚጨምር የመማር ልምዶችን ያቀርባል።
    - ስርዓተ ትምህርቱን የሚደግፍ፤ ለእያንዳንዱ ተማሪ ተስማሚ-ሆኖ የሚስሩትን ቴክኒኮች እና ቁሳቁሶች (techniques and materials)ን መጠቀም እና መወሰን።
    - ለተማሪዎቻችን፣ የሚጠበቅባቸውን ከፍተኛ-ደረጃ ያለውን መማር - ጠብቀው-እንዲሰሩ ማድረግ።
    - ከወላጆች ጋር አጋርነትን-በመፍጠር፣ ልጆቻቸውን በትምህርታቸው ላይ ለመርዳት የሚችሉበትን መንገዶች፤ እንደ - በትምህርት ገበታ መገኘትን መቆጣጠር፣ ማንበብና መፃፍ፣ እና የቴክኖሎጂ ስልጠናን፣ እንደ አስፈላጊነቱ፤ የወላጆች ተሳትፎን ለማስፋፋት፣ ከልጆቻቸው ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን

ውሳኔዎች ውስጥ ለመካፈል እንዲችሉ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች (extracurricular) ላይ ያላቸውን ጊዜ በመጠቀም ላይ አዎንታዊ-በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸውን መንገዶች ያቀርባል።

- ዓመታዊ ስብሰባ ማካሄድ - ተካፋይ-ለሆኑ ልጆች-ወላጆች - አመቺ የሆነውን ጊዜ መርጦ፣ የትምህርት ቤታቸውን በ'Title I' ውስጥ መካፈልን፣ የ'Title I' መስፈርቶችን፣ ለመካፈል ወላጆች ስለአላቸው መብቶች፣ እና የPAFE የእርዳታ-ገንዘብን በመጠቀም-ላይ ያላቸውን አስተያየት መጠየቅ ላይ፤ ለወላጆች ለማሳወቅ ማካሄድ። የዚህ-ዓመት፣ የ'Title I' ምሽት፣ ሴፕቴምበር (September) 9 ቀን 2025 ላይ እንዲካሄድ - የጊዜ-ሰሌዳ ተይዞለታል። ሁሉም ወላጆች የተጋበዙ እና እንዲሳተፉም ይበረታታሉ።

- የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎችን - በዓመት ሁለት-ጊዜ ማካሄድ፤ በዚህ ጥምረት **(compact)** ወቅትም፤ ከእያንዳንዱ ልጅ የግል ስኬታማነት ጋር በተያያዘ-ሁኔታ ውይይት ይደረጋል።
  - የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፣ በ10/13/25, 02/25/26, እና 03/04/26 ይካሄዳሉ።
  - ስጋት ወይም አስፈላጊነት እንዳለው፣ ወላጅ ወይም አስተማሪ እንዲደረግ ከጠየቁ፤ ኮንፈረንሶቹ በማንኛውም ጊዜ ሊካሄዱ ይችላሉ።

- ስለልጆቻቸው የእድገት ሂደቶች፤ በየጊዜው ሪፖርቶችን ለወላጆች ማቅረብ። በተለይ-ደግሞ፣ ትምህርት ቤቱ - በሚከተለው-ሁኔታ ሪፖርቶችን ያቀርባል:
  - በእያንዳንዱ የቀለም ትምህርት አጋማሽ (academic quarter) መጨረሻ ላይ፣ ሪፖርት ካርድ ወደ ቤት ይላካል። ከሚከተሉት አጋማሽ (quarter) መጨረሻ-ቀናቶች በኋላ፣ ሪፖርት ካርዶች ወደ መኖሪያ-ቤት ይላካሉ: ኦክቶበር (October) 31 ቀን፣ ጃንዋሪ (January) 22 ቀን፣ ማርች (March) 27 ቀን፣ እና ጁን (June) 12 ቀን።
  - ወላጆች፤ በኢሜል፣ ቴክስት (text) መልዕክቶች፣ እና/ወይም በስልክ ጥሪዎች አማካኝነት፣ የልጆቻቸውን የእድገት-ሂደቶችን የሚያሳዩ ሪፖርቶችን ለማግኘት፣ ጥያቄ ባቀርቡ ጊዜም፣ ይሠጣቸዋል።

- በትምህርት ቤቱ የ**'Title I'** ፕሮግራም፤ ዕቅድ አወጣጥ፣ ምልከታ፣ እና ማሻሻያ ላይ፤ ወላጆችን በተቀናጀ፣ በቀጣይነት፣ እና ጊዜውን በጠበቀ መንገድ ማሳተፍ።

## የርዕሰ መምህሩ/የአስተዳደራዊ ቡድን ስምምነት

የ'ጄፈርሰን ሂውስተን/**Jefferson Houston** ከ**PRE K-8** ትምህርት ቤት' ርዕሰ መምህር/አስተዳደራዊ ቡድን፣ የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- የቤተሰብ ተሣትፎ ፖሊሲ (Family Engagement Policy)ን፣ ማጎልበት እና አፈፃፀሙን መደገፍ።
- ለመማር ሂደቱ፣ መልካም የሆነ አካባቢን እንዲኖር ማጎልበት።
- በአስተማሪዎች፣ ወላጆች እና ተማሪዎች መካከል ግንኙነትን-ለማድረግ የሚያስችሉትን-ሁኔታዎችን - ማጎልበት።
- የትምህርት እንቃስቃሴዎች፣ ኮሚቴዎችን እና ፕሮግራሞችን መደገፍ እና መካፈል።

## የትምህርት ቤት ሠራተኞች - ስምምነት

የ'ጄፈርሰን ሂውስተን/**Jefferson Houston** ከ**PRE K-8** ትምህርት ቤት' ሠራተኞች - የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- በልጁ ትምህርት ላይ አጋር-የምንሆንበትን - እንክብካቤ-ያለው የመማሪያ አካባቢን ማቅረብ።
- ለቤተሰቦች አመቺ የሆነ መልካም መስተንግዶ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማጎልበት።
- የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን መደገፍ እና መሳተፍ።
- ከACPS የስርዓተ-ትምህርት፣ የቨርጂኒያ የስቴት መደበኛዎች (Virginia State Standards) እና የዓለም-አቀፍ ባካሎሪየት ማዕቀፍ (International Baccalaureate framework) ጋር ጎን-ለጎን በሚሄድ

ሁኔታ፣ የበለፀገ እና የበለጠ-እንዲሰሩ ሊፈትናቸው የሚችል - ስርዓተ-ትምህርትን ማቅረብ።

- ጤናማ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ የመማር ሂደትን ሊያጎለብት የሚችል፣ ተንከባካቢ የመማሪያ አካባቢን ማቅረብ።
- የኮሌጅን እና የስራ-መስክ ዝግጁነትን ለማበረታታት የሚችል አካባቢን ማጎልበት።

## <u>የወላጅ/የአሳዳጊ ስምምነት</u>

የ'ጀፈርሰን ሂውስተን/**JEFFERSON HOUSTON** ከ**PRE K-8** ትምህርት ቤት' ወላጆች/አሳዳጊዎች - የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- በሰዓቱ፣ በመደበኛነት የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትን፣ አጽንዖት ይሰጣል።
- ስለልጆቻቸው የየቀኑ የትምህርት ውሎ እና ምን እንደተማሩ መጠይቅ።
- ሁሉንም የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) በጊዜው ማጠናቀቅን፣ አጽንዖት ይሰጣል።
- በወላጆች- አስተማሪ ኮንፈራንሶች አማካኝነት እና/ወይም በ'PowerSchool' እና ካንቫስ (Canvas) ላይ በሚደረጉ አዲስና ማሻሻያዎች (updates)፤ መደበኛ የትምህርት ቤት ግንኙነቶችን መጠበቅ።
- በእያንዳንዱ ዓመት፣ ቢያንስ በአንድ የትምህርት ቤት ዝግጅት ውስጥ ለመካፈል ጥረት ማድረግ (ማለትም፤ በPTA፣ በ'Back to School' ምሽት፣ የትምህርት ቤት ኮንሰርቶች፣ የርዕሰ-መምህር ቡና/Principal Coffees፣ ለሁሉም ክፍት የሆነ ዝግጅት/Open House፣ ወዘተ...)

## <u>የተማሪ ስምምነት</u>

የ'ጀፈርሰን ሂውስተን/**JEFFERSON HOUSTON** ከ**PRE K-8** ትምህርት ቤት' ተማሪዎች - የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- ትምህርት ቤት በመደበኛነት ተገኝቶ መማር እና በሰዓቱ መገኘት።
- በየትምህርት ዓይነት በየክፍል ትምህርት ምን እንደሚጠበቅ፣ ማወቅ።
- ወጥነት-ባለው የ'ROARS' ማሳያ አማካኝነት፣ የ'Jaguar Pride'ን ምሳሌያዊ-አርአያነት ለማሳየት-መጣር • ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ስለትምህርታቸው ለማወቅ ጉጉት-ማሳየት።
- በትምህርታቸው ውስጥ በንቃት መገኘት እና መሳተፍ፣ እና ሁሉንም የቤት/የክፍል ስራዎችን (assignments) ማጠናቀቅ። • ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ፣ ለመማር ተዘጋጅተው - አስፈላጊ የሆኑ የመማሪያ ዕቃዋች በመያዝ እና/ወይም የመማሪያ ዕቃዎች ሲያስፈልጓቸው ለራሳቸው ተከራካሪ ሆኖ-መቆምን እንዲማሩ (ለምሳሌ፤ ክሮምቡክ/chromebook፣ አጀንዳ ደብተሮች (agenda books) እስክሪብቶዎች፣ እርሳሶች፣ ባይንደሮች/binders. ወዘተ...

### የ**ACPS** ስርዓተ ትምህርት ዝርዝር መግለጫ

| | |
|---|---|
| <u>የእንግሊዘኛ የቋንቋ ስነጥበታት **(English Language Arts)**</u><br>በ'ELA' የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዋች፤ እንዴት መግባባት፣ ማንበብ፣ መፃፍ እና ምርመራ **(research)** ማድረግን፣ በዓመቱ-በሙሉ ይማራሉ። | <u>ሂሳብ **(Mathematics)**</u><br>ተማሪዎች፤ በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃቸው ውስጥ፤ የቁጥሮችን እና ሂሳብ ስሌትን መረዳት፣ ልኬት/**measurement**፣ ጂኦሜትሪ፣ አልጄብራ እና የመረጃ-ስብስብ **(data)** ትንታኔ እና የመሆን-ሁኔታ **(probability)** ላይ፣ ትኩረት ያደርጋሉ። |
| <u>ሣይንስ **(Science)**</u><br>ተማሪዎች፤ ሣይንሳዊ መግለጫዎችን - ለማሳደግ፣ ለማጣራት፣ እና በስራ-ላይ ለማዋል፤ ማስረጃን ይፈጥራሉ እና ይጠቀማሉ። ተማሪዎች - በመጠየቅ-ላይ መሠረት ባደረገ መማር ውስጥ - በእጅ-በመሞከር የሚሰሩትን/hands-on experience | <u>ጎብረ ትምህርት **(Social Studies)**</u><br>የአገራችንን የወደፊት-ሁኔታ ለመቅረጽ እንዲቻል፣ ተማሪዎች ያለንን ብሄራዊ ቅርሶች ይረዳሉ። ተማሪዎች፣ ታሪካዊ ክስተቶችን፣ ህዝቦችን፣ እና ቦታዎችን መተንተን እና መግለጽን፣ እንዲችሉ ይማራሉ። አስተማሪዎች፤ የሲቪክ-አስተሳሰብ ያለው፣ ዲሞክራሲያዎ ማህበረሰብ |

| | |
|---|---|
| (ማለትም labs)ን ጨምሮ፣ ይሳተፋሉ። | እንዲኖር ያበረታታሉ። |
| **'ELECTIVES'** | |
| • **የዓለም ቋንቋዎች/World Languages: ተማሪዎች፤** ከእንግሊዘኛ ውጭ - በሌላ ቋንቋ ለመገንዘብ እና መግባባት የሚችሉ ይሆናሉ። ተማሪዎች፣ በውጪ-ሃገር ቋንቋ የመማሪያ ክፍሎቻቸው ውስጥ፣ በሌሎች የትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሚያገኟቸውን - ችሎታዎች እና እውቀትን ይማራሉ። የዓለም ቋንቋ (World Language) ኮርሶች፤ ተማሪዎች - አሁንም በመካከለኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ፤ ለከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ክሬዲትን ለማግኘት ዕድል ይሰጣቸዋል። | • **AVID:** አስተማሪዎች፤ በዓለም-ዓቀፍ ማህበረሰብ ውስጥ፣ ተማሪዎችን ለኮሌጅ ዝግጁነት እና ስኬት ያሰናዷቸዋል። የስርዓተ-ትምህርቱ፤ መፃፍ፣ መጠየቅ፣ ትብብርን፣ ንባብ፣ ማስታወሻ-አያያዝ፣ እና የማጥናት ችሎታዎች፣ እና የኮሌጅ/የስራ-መስክ/የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎችን ያንፀባርቃል። |

| | |
|---|---|
| • ስነጥበብ/**Art:** ተማሪዎች፤ የግል ሃሳቦችን፣ ልምዳቸውን እና በስነጥበብ (art) ስራዎች ውስጥ ትረካዎችን፤ በፈጠራዊ አስተሳሰብ፣ ግንኙነት ለማደረግ ይጠቀማሉ። ተማሪዎች የስነጥበብ ስራ (artwork)ን፤ መተንተን፣ መተርጎም፣ እና መገምገም ይችላሉ። አስተማሪዎች፣ ከስነጥበብ-ባለሞያ ህብረተሰብ ጋር ለመግባባት የሚያስችል፣ የግንኙነት-ማድረጊያ እና የትብብር ችሎታን ለማሳደግ እንዲችሉ ተማሪዎችን ያግዛሉ።<br><br>• ባንድ/ኦርኬስትራ **(Band/Orchestra):** ተማሪዎች፤ በዘፈን፣ የሙዚቃ-መሳሪያ በመጫወት፣ ዜማዎችን ማቀናበር (performing rhythms)፣ ወደ ዜማዎች መዛወርን፣ እና ሙዚቃን መፍጠር ባሉት ተሞክሮዎች አማካኝነት፤ የሙዚቃ እውቀትና ችሎታቸውን ይገነባሉ። ተማሪዎች፣ የሙዚቃ ተግባርን ለማወዳደርና ለማነፃፀር እንዲሁም ሙዚቃ በህብረተሰብ ላይ የሚፈጥረውን ተፅዕኖ በማጥናት፣ አመዛዝኖ የማሰብ ችሎታቸውን ይጠቀማሉ። አስተማሪዎች፤ ተማሪዎችን - ከተለያዩ የባህል-ተጽዕኖዎች፣ ስታይሎች (styles)፣ አቀናባሪዎች እና የታሪካዊ ወቅቶች ውስጥ ነበሩ የሙዚቃ ዓይነቶችን፣ እንዲያውቁዋቸው ያደርጋሉ።<br><br>• የአካል-ብቃት ትምህርት **(Physical Education)**: ተማሪዎች የጤና መሠረታዊ-ሁኔታዎችን፤ ለመለየት እና አስፈላጊ የሆኑ ጤና ይዘቶችን ለመገለፅ እና የግል ጤናን እና ጤናማ የሆነ ልምዶችን ያዳብራሉ። | • የቴክኖሎጂ እና ኢንጂነሪንግ/**Technology and Engineering** ትምህርት: ተማሪዎች የኢንጂነሪንግ ዲዛይን ሂደትን በመጠቀም - ችግሮችን ይለያሉ እና መፍትሄ-ይሰጣሉ።<br>○ **6ኛ** ክፍል: ወደ ቴክኖሎጂ እና ኢንጂነሪንግ/Technology and Engineering - ማስተዋወቅ<br>○ **7ኛ** ክፍል: አዲስ-ግኝቶች እና ፈጠራዎች (Inventions and Innovations)<br>○ **8ኛ** ክፍል: ቴክኖሎጂያዊ ስርዓቶች (Technological Systems)<br><br>**የልዩ ፕሮግራሞች (Special Programs)**<br><br>• ዓለም-አቀፍ ባካሎሪየት/**International Baccalaureate**: የመጀመሪያ እና መካከለኛ/Primary and Middle የዓመታት ፕሮግራሞች/Years Programs<br><br>• የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ **(English Learner):** የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ (English Learner (EL) ፕሮግራም፤ ስብጥር ካለው የባህል የቀድሞ-መነሻ (backgrounds) የመጡ ተማሪዎችን - ትምህርት ለማሻሻል የተቀረጸ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ፤ የ'EL' ተማሪዎች የቀደመውን ቋንቋቸውን፣ የቀድሞ-መነሻ እውቀታቸውን፣ እና ልምዶቻቸውን የሚያከብር ነው። የ'EL' ተማሪዎች፤ የቀለም ትምህርት ቋንቋን በቅልጥፍና እንዲያሳድጉ እንዲረዳቸው፤ በዓመቱ-ሙሉ ውስጥ፣ የተለየ የትምህርት-አሰጣጥን ያገኛሉ።<br><br>• የላቀ-ደረጃ ያለው የቀለም-ትምህርት አገልግሎቶች/**Advanced Academic Services (AAS)** |

| | |
|---|---|
| | • **የልዩ ትምህርት (Special Education) ፕሮግራሞች** |